በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

የቦሌ ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት የ **2015** ዓ.ም

የ **6** ኛ ክፍል የአካባቢ ሳይንስ ትም/ት ሞዴል ፈተና

የጥያቄ ብዛት፡- **40**

የተፈቀደው ሰዓት፡- **1** ሰዓት

አጠቃላይ ትዕዛዝ

ይህ የአካባቢ ሳይንስ ፈተና ነው። በዚህ ፈተና ውስጥ **40** ጥያቄዎች ተካተዋል፤ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ የሆነውን አማራጭ የያዘውን ፊደል በመምረጥ ለመልስ መስጫ በተሰጠው ወረቀት ላይ በማጥቆር መልስ ይሰጣል። በፈተና ላይ የተሰጡትን ትዕዛዞች በጥንቃቄ በማንበብ ፈተናውን መሥራት ይጠበቅባችኋል። መልስ የሚሰጠው ከፈተናው ጋር በተያያዘው የመልስ መስጫ ወረቀት ላይ ነው። በመልስ መስጫው ላይ ትክክለኛው መልስ የሚጠቁረው በእርሳስ ብቻ ነው። ትክክለኛውን መልስ ለማጥቆር ሚሰራ ለማጥቆር የተፈቀደው ቦታ በሙሉ በሚታይ መልኩ በደንብ መጥቆር አለበት። የጠቆረውን መልስ ለመቀየር ቢፈለግ በፊት የጠቆረውን

በደንብ በማጥፋት መጽዳት አለበት።

ፈተናውን ሠርቶ ለመጨረስ የተፈቀደው ሰዓት **1** ሰዓት ነው። ፈተናውን ሠርቶ ለመጨረስ የተሰጠው ሰዓት ሲያበቃ ለመሥሪያነት የምንጠቀምበትን የመጻፊያ እርሳስ ማስቀመጥና ፈተናውን መሥራት ማቆም አለባቹ። ፈተናው እንዴት እንደሚሰበሰብ በፈታኙ/ኟ እስከሚነገር ድረስ በቦታችሁ ተቀምጣችሁ መጠበቅ አለባችሁ።

የሚኮርጅ ወይም በፈተና ሰዓት የፈተናን ህግ የማያከብር ተፈታኝ ፈተናው አይያዝለትም፤ ፈተናውን


እንዳይፈተንም ይደረጋል።

ፈተናውን መሥራት ከመጀመራችሁ በፊት በመልስ መስጫው ላይ መሞላት የሚገባው መረጃ ሁሉ በጥንቃቄ

መሞላት አለበት።

ፈተናውን ጀምሩ ሳይባል መጀመር አይፈቀድም!

ከተራ ቁጥር 1 እስከ 2 ለቀረቡት ጥያቄዎች ከዚህ በታች በተቀመጠው አብይ ትይዩ መስመሮችን የሚያሳይ ምስልን መሰረት በማድረግ መልሱ።



66 ½^0 ሰ

23 ½^0 ሰ

0^0

23 ½^0 ደ

66 1/2^0 ደ

1. ከላይ በምስሉ ላይ ፊደል "a" የሚወክለው አብይ ትይዩ መስመር ምን ይባላል?
   ሀ . የካንሰር መስመር ሐ. የካፕሪኮርን መስመር
   ለ. የአርክቲክ መስመር መ . የአንታርክቲክ መስመር
2. ከላይ በምስሉ ላይ የካፕሪኮርን ሞቃታማ የሐሩር መስመር የሚወክለው ፊደል የቱ ነው?
   ሀ. d ለ. a ሐ. b መ. c
3. ከሚከተሉት ውስጥ አንዷ የምስራቅ አፍሪካ ቀንድ ሀገር አይደለችም።
   ሀ. አትዮጵያ ለ. ኤርትራ ሐ. ታንዛንያ መ. ጅቡቲ
4. ከሚከተሉት የምስራቅ አፍሪካ ተራሮች መካከል በከፍታ ትልቁ የቱ ነው?
   ሀ. የሩዋንዞሪ ተራራ ለ. የኬንያ ተራራ ሐ. የሜሩ ተራራ መ. የራስ ዳሽን ተራራ
5. ከሚከተሉት ውስጥ የምስራቅ አፍሪካ አጎራባች ሀገር ያልሆነችው የትኛዋ ናት?
   ሀ. አንጎላ ለ. ቦትስዋና ሐ. ማሊ. መ. ስዋዚላንድ
6. ከሚከተሉት ውስጥ በየብስ፣በመኪና እና በአየር ላይ የሚንቀሳቀሱ አካላት አቅጣጫን ለመጠቆም የሚያግዘን መሳርያ ወይም መተግበሪያ የቱ ነው?
   ሀ. ጂፒኤስ ለ. ጎግል ኧርዝ ሐ. ቴሌስኮፕ መ. ጎግል ካርታ
7. ከሚከተሉት ውስጥ ተመራማሪዎች ሩቅ ያሉ ቦታዎችን ለማየት እና ለመመርመር እንዲሁም ስለ ተለያዩ በሽታዎች መከሰት ትንበያ ለመስጠት የሚያስችላቸው መተግበሪያ ምን ይባላል?
   ሀ. ጎግል ካርታ ለ. ጎግል ኧርዝ ሐ. ጂፒኤስ መ. ማይክሮስኮፕ
8. ከሚከተሉት የደም ህዋሶች ውስጥ በቁጥር ከፍተኛ የሆነው የቱ ነው?
   ሀ. ቀይ የደም ህዋስ ለ. ፕሌትሌቶች ሐ. ነጭ የደም ህዋስ መ. ደም ቅዳ
9. ከሚከተሉት ውስጥ ከቀኝ ተቀባይ ልበ ገንዳ የተቀበለውን በኦክስጅን ያልበለፀገ ደም በፑልምናሪ አርተሪ ወደ ሳንባ የሚረጨው የልብ ክፍል የቱ ነው?
   ሀ. ቀኝ ተቀባይ ልበ ገንዳ ሐ. ግራ አቀባይ ልበ ገንዳ
   ለ. ግራ ተቀባይ ልበ ገንዳ መ. ቀኝ አቀባይ ልበ ገንዳ
10. ምንም ያልተዛባ የወር አበባ የምታይ ሴት የመጀመርያውን የወር አበባ ግንቦት 8 ቀን ብታይ ቀጣዩን የወር አበባ መቼ ልታይ ትችላለች?
    ሀ. ግንቦት 28 ለ. ሰኔ 14 ሐ. ሰኔ 5 መ. ሰኔ 28
11. ኦክስጅን ከሳንባ ወደ ደም እና ካርቦንዳይ ኦክሳይድ ከደም ወደ ሳንባ የሚተላለፍበት የመተንፈሻ አካል ምን ይባላል?

ሀ. ደቂቅ ቧንቧ ለ. ድህረ አፍ ሐ. ዋና የአየር ቧንቧ መ. የአየር ከረጢት

12. ወደ ውስጥ ከምናስገባው በፐርሰንት ክፍተኛ ሆኖ ወደ ውጭ ስንተነፍስ ደግሞ ዝቅተኛ ሆኖ የሚወጣው የአየር ምንዝር ምን ይባላል ?

ሀ. ካርቦንዳይ ኦክሳይድ ለ. ኦክስጅን ሐ. ናይትሮጂን መ. የውሃ ትነት

13. ከሚከተሉት ድብልቆች መካከል የድብልቁ ይዘት ወጥ እና ተመሳሳይ የሆነው የቱ ነው ?

ሀ. ደም ለ. ወተት ሐ. የጨው ሙሙት መ. የአሸዋና የውሃ ድብልቅ

14. በአሸዋና እና በስኳር ሙሙት ድብልቅ ውስጥ ስንት ምንዝሮች አሉ?

ሀ. 2 ለ. 4 ሐ. 3 መ.5

15. ሁለት ፈሳሾች ባላቸው የነጥበ ፍሌት ልዩነት የምንለይበት የመለያ ዘዴ ምን ይባላል?

ሀ. ንጥረት ለ. ትነት ሐ. ጥልያ መ. ቀረራ?

16. ከሚከተሉት ውስጥ ታዳሽ ያልሆነው የጉልበት ምንጭ የቱ ነው?

ሀ. የባትሪ ድንጋይ ለ. የፀሐይ ብርሃን ሐ. ውሃ መ. ንፋስ

17. ክብደት ያላቸውን ነገሮች ለመጫን የሚጠቅመን የቀላል መኪና ዓይነት የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ሽብልቅ ለ. መፈንቅል ሐ. መፍቻ መ. ዘንባይ ወለል

18. አመቱን ሙሉ ከፍተኛ ሙቀት እና የዝናብ መጠን ያለው የአየር ንብረት ክልል የቱ ነው?

ሀ. የደጋ የአየር ንብረት ክልል

ለ. የሐሩር ሞቃታማ የባህር ዳርቻዎች የአየር ንብረት ክልል

ሐ. የበረሃ የአየር ንብረት ክልል

መ. የሳር ምድር ሞቃታማ የአየር ንብረት ክልል

19. ከሚከተሉት መካከል የአየር ንብረት ተቆጣጣሪዎች ውስጥ የማይመደበው የቱ ነው?

ሀ. ከምድር ወገብ ያለው ርቀት ሐ. የቅዝቃዜ መጠን

ለ. የውቅያኖስ ሞገድ መ. ከባህር ያለው ርቀት

20. ከሚከተሉት ውስጥ በወርቅ እና በቆርቆሮ ማዕድናት ዓይነቶች የምትታወቅ ሀገር የትኛዋ ናት?

ሀ. ቡሩንዲ ለ. ዩጋንዳ ሐ. ኢትዮጵያ መ. ታንዛኒያ

21. ከሚከተሉት ውስጥ የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ ዘዴ የማይመደበው የቱ ነው?

ሀ. ታዳሽ የኃይል ምንጮችን መጠቀም ሐ. ሀገር በቀል ዕፅዋትን ማስወገድ

ለ. የተፈጥሮ ሀብትን በአግባቡ መጠቀም መ. ባዮ ጋዝን መጠቀም

22. ከሚከተሉት የአፈር አይነቶች መካከል በኢትዮጵያ የሚገኙት የትኞቹ ናቸው?

ሀ. ዜሮሶል እና ሊቶሶል ሐ. ፈራሶል እና አክሪሶል

ለ. ካምቢሶል እና ላቪሶል መ. የርሞሶል እና ሶላንቻክ

23. ደን ባልነበረበት ዛፎችን ማብቀል እንዲሁም ዕፅዋት ባልነበሩበት ስፍራ ችግኞችን የመትከል ተግባር ምን ይባላል?

ሀ. ደግም ድንና ለ. የእርከን ስራ ሐ. ዘር ማፈራረቅ መ. ድንና

24. ከሚከተሉት ውስጥ ከስምጥ ሸለቆ ውጭ ያሉ ሀይቆች የማይመደበው የቱ ነው?
ሀ. ቪክቶርያ ሀይቅ ለ. የታንጋኒካ ሀይቅ ሐ. የቱርካና ሀይቅ መ. የአልበርት ሀይቅ

25. ከሚከተሉት ወንዞች መካከል ወደ ህንድ ውቅያኖስ የማይገባው የቱ ነው?
ሀ. የዋቢ ሸበሌ ወንዝ ለ. የዛምቤዚ ወንዝ ሐ. የታና ወንዝ መ. የገናሌ ወንዝ

26. ከሚከተሉት ውስጥ በኢትዮጵያ፣በኤርትራ እና በጅቡቲ መካከል በሚገኝ ባለ ሶስት ማዕዘን ወሰን ላይ የሚገኝ ስነ ምህዳር የቱ ነው?
ሀ. ማሳይ ማራ ሐ. የብዊንዲ ጥቅጥቅ ደን ብሔራዊ ፓርክ
ለ. የደንከል በረሃ መ. የሰሜን ተራራ ብሔራዊ ፓርክ

27. ከሚከተሉት ውስጥ ከማዕከላዊ አፍሪካ አካባቢ ምስራቅ አፍሪካን የምታዋስን ሀገር የትኛዋ ናት?
ሀ. ሱዳን ለ. ቦትስዋና ሐ. ደቡብ አፍሪካ መ. አንጎላ

28. ከሚከተሉት አንዱ የህዝብ ባህሪያት መገለጫ አይደለም።
ሀ. የህዝብ ስርጭት ሐ. የቴክኖሎጂ ዕድገት
ለ. የህዝብ ዕድገት ምጣኔ መ. የህዝብ ብዛት

29. የአስመራ ከተማ በዩኒስኮ የተመዘገበችበት ዋና ምክንያት የሆነው የቱ ነው?
ሀ. የበርካታ ህዝብ መኖሪያ ስለሆነች
ለ. ከባህር ወለል በላይ 2000 ሜትር ከፍታ ስለምትገኝ
ሐ. የዕድሜ ጠገብ ህንፃዎች ባለቤት ስለሆነች
መ. በኢጣሊያን ቅኝ ግዛት ስር ስለነበረች

30. ከሚከተሉት ውስጥ የቅርስ ምጣኔ ሀብታዊ ፋይዳ ያልሆነው የቱ ነው?
ሀ. የፈጠራ ስራን ለማጎልበት
ለ. አለም አቀፍ የንግድ ግንኙነትን ለማቋረጥ
ሐ. የወደፊት የዕድገት አቅጣጫን ለመተንበይ
መ. የምጣኔ ሀብት አቅምን ለማሳደግ

31. በምስራቅ አፍሪካ የቅርሶች አጠቃቀም ከሚቀንሱ ምክንያቶች ውስጥ የማይመደበው የቱ ነው?
ሀ. ብቁና የሰለጠኑ አስጎብኝዎች መኖር ሐ. ለተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ አደጋዎች መጋለጥ
ለ. በቂ የሆነ እንክብካቤ አለመኖር መ. በሰዎችና እንስሳት መረገጥ

32. ከላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት መካከል ለብቻው በምዕራባዊ አቅጣጫ የሚገኘው ቤተ ክርስቲያን ማን ይባላል?
ሀ. ቤተ ማርያም ለ. ቤተ ሚካኤል ሐ. ቤተ ጊዮርጊስ መ. ቤተ ደናግል

33. ከሚከተሉት ውስጥ በምስራቅ አፍሪካ የቱሪዝም ምጣኔ ሀብታዊ ጠቀሜታ ያልሆነው የቱ ነው ?
ሀ. የዕደ ጥበብ ስራዎችን እና ውጤቶችን ለማበረታታት
ለ. የመንግስትን የውጭ ምንዛሬ ለመጨመር
ሐ. ከውጭ ሀገራት ጋር ያለውን ግንኙነት ለማዳከም
መ. የስራ ዕድልን ለማመቻቸት

34. የተለያዩ አትክልቶችን ፣ፍራፍሬዎችና አበባዎችን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ የማምረት ዘዴ ምን ይባላል?
ሀ. ኢንዱስትሪ ለ. ሆርቲካልቸር ሐ. ንግድ መ. ቱሪዝም

35. የምስራቅ አፍሪካ የልማት በይነ መንግስታት ድርጅት መቀመጫ ሀገር የት ነው ?
ሀ. ጅቡቲ ለ. ኢትዮጵያ ሐ. ሶማሊያ መ. ዩጋንዳ

36. ከሚከተሉት መካከል ኤች አይ ቪ/ኤድስን ለመከላከል ከሚያስፈልጉ የህይወት ክህሎት መርሆች የማይመደበው የቱ ነው?
ሀ. ራስን መግዛት ለ. በራስ መተማመን ሐ. ስሜታዊ መሆን መ. ጭንቀትን መቋቋም

37. ከሚከተሉት መካከል በጫት ውስጥ የሚገኘው ኬሚካል የቱ ነው?

ሀ. ኢታኖል ለ. ትንባሆ ሐ. ኒኮቲን መ. ካቴኒን

38. ከሚከተሉት አንዱ የሴት ልጅ ግርዛት የሚያስከትለው ችግር አይደለም።

ሀ. ከፍተኛ የደም መፍሰስ ሐ. ለስነ ልቦና ችግር ያጋልጣል

ለ. በወሊድ ጊዜ ምጥ እንዲቀንስ ያደርጋል መ. በብልት ላይ ጠባሳ ይፈጥራል

39. ከሚከተሉት ውስጥ ከጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች የማይመደበው የቱ ነው?

ሀ. ግግ ማስወጣት ለ. ያለእድሜ ጋብቻ ሐ. ጠለፋ መ. የወንድ ልጅ ግርዛት

40. ከሚከተሉት ውስጥ በምስራቅ አፍሪካ ለድርቅ ምክንያት የሆነው የቱ ነው?

ሀ. የአየር ንብረት ለውጥ ሐ. የህዝብ ቁጥር መቀነስ

ለ. የኢንዱስትሪ አለመስፋፋት መ. የእርሻ ቦታ አለመስፋፋት